Arlington Public Schools

**የበልግ 2021 የድንበር ሂደት ፡- የቅድረ ማጽደቅ ማሳወቂያ ደብዳቤ**

## በዕቅድ ዩኒቶች 46110፣ 46120፣ 46111፣ 48160፣ 48180፣ 48290፣ 46140፣ 48150፣ 48280፣ 48281 ነዋሪ ለሆኑ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ቤተሰቦች

ዲሴምበር 10 ቀን 2021

ውድ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ቤተሰቦች፡-

የትምህርት ቤቱ ቦርድ በዲሴምበር 2 ቀን 2021 ባካሄደው ሰብሰባ ከኦገስት 2022 ጀምሮ ተፈጻሚነት የሚኖረውን የበልግ 2021 የድንበር ማሻሻያ በማጽደቅ ድምጽ ሰጥቷል፡፡

የ46110፣ 46120፣ 46111፣ 48160፣ 48180፣ 48290፣ 46140፣ 48150፣ 48280፣ 48281 የዕቅድ ዩኒቶች ከ2022-23 የትምህርት ዘመን ጀምሮ ከዌክፊልድ ወደ ዋሽንግተን-ሊበርቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመድበዋል፡፡ ይህ ለውጥ ለሁሉም አዲስ ገቢ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች (በ2021-22 የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች) እንዲሁም ከላይ በተዘረዘሩት የዕቅድ ዩኒቶች ውስጥ ነዋሪ ለሆኑ የወደፊት አዲስ ገቢ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ በዱዋል ቋንቋ ኢ-መርሽን ፕሮግራም ወይም በሞንቴሶሪ ፕሮግራም ያሉ ተማሪዎች እነዚህን ፕሮግራሞች በዌክፊልድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መቀጠል ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ከላይ ከተዘረዘሩት የዕቅድ ዩኒቶች መካከል በአንዱ ነዋሪ የሆኑ እና በአሁኑ ጊዜ በዌክፊልድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ወይም ከጁን 17 ቀን 2021 በፊት በዌክፊልድ የሚገቡ የ9ኛ - 11ኛ ክፍል ተማሪዎች የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ በዌክፊልድ መቀጠል ወይም በ2022-23 አዲስ በተመደቡበት የአካባቢው ትምህርት ቤት (ዋሽንግተን-ሊበርቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) መቀጠል ይችላሉ፡፡

**ወንድምና እህቶች፣ እና የትራንስፖርት መረጃ**

- **ወንድሞችና እህቶች፡-** በገንስተን የ9ኛ -11ኛ ክፍል ተማሪዎች ወንድሞች/ እህቶች የሆኑ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ ከላይ ከተዘረዘሩት ዩኒቶች በአንዱ ነዋሪ የሆኑ በ2022-23 የትምህርት ዘመን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገቡ ከታላላቅ ከወንድሞቻቸው ወይም እህቶቻቸው ጋር በዌክፊልድ አብረው መማር እንዲችሉ ሊዘዋወሩ ይችላሉ፡፡ ለእነዚህ ቤተሰቦች ራሱን የቻለ ደብዳቤ እና ቅጽ ይላካሉ፡፡

- **ትራንስፖርት ፡-** የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ከላይ በሚገኙት የዕቅድ ዩኒቶች ውስጥ ያሉ ነገር ግን በእግር ከሚደረስበት ዞን ውጪ ነዋሪ ለሆኑ ተማሪዎች በዋሽንግተን-ሊበርቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (አዲስ የተመደበ የአካባቢው ትምህርት ቤት) ትራንስፖርት ያቀርባል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች/ ፕሮግራሞች አማራጭ ለሚከታተሉም በአገር አቀፍ ሀብ ስቶፕ አማካኝነት የአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ትራንስፖርት ይቀርባል፡፡

ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት፣ ተመራጩ ጥያቄዎን የማቅረብ ዘዴ በengage@apsva.us ኢሜል ማድረግ ወይም በስልክ ቁጥር 703-228-2481 የዕቅድ እና ግምገማ ክፍልን ማነጋገር ነው፡፡ የበልግ 2021 የድንበር ሂደትን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ከዚህ የሚከተለውን ሊንክ ይጎብኙ፡- https://www.apsva.us/engage/fall-2021-boundary-process፡፡

አመሰግናለሁ፣

ሊሳ ስቴንግል
የዕቅድ እና ግምገማ ዳይሬክተር
አርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች